# መቅደላ

የዐማራ ኅልውና ለኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (ዐኅኢአድ) ልሣን

Amara Survival for Ethiopian Unity Organization (ASEUO)



የዐማራ ኅልውና መጠበቅ፣ ለኢትዮጵያ አንድነት መጠበቅ ዋስትና ነው!

ፈለገ አሥራት የትውልዳችን ቃል ኪዳን ነው!

ቅጽ: ፪ ቁጥር: ፪ ቀን: ሰኔ ፳፬

በየ15ቱ ቀን ዘወትር ኀሙስ የሚወጣ


## የዐማራው ጥያቄዎች የሚመለሱት በራሱ ዐማራው ትግል ነው!

የዐማራ ኅልውና ለኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (ዐኅኢአድ) ለመመሥረት ምክንያት ከሆኑት መሠረታዊ ጉዳዮች መካከል አንዱ፡- በዐማራው ነገድ ላይ እየተፈጸመ ያለው የዘር ማጥፋትና የዘር ማጽዳት ድርጊት መንግሥታዊ መዋቅርን ተከትሎ የመፈጸሙና በትግሬ-ወያኔው የተረቀቀውና ፀደቀ የተባለው ሕገመንግሥት ዐማራውን አገር አልባ በማድረጉ ነው። የድርጅቱ መሠረታዊ ዓላማም በዐማራው ላይ የተከፈተውን የዘር ማጥፋትና ማጽዳት ድርጊት ማስቆም፣ በዐማራው ላይ የዘር ማጥፋት እና ማጽዳት ወንጀል የፈጸሙ ግለሰቦችና ቡድኖችን ለፍትሕ ማቅረብ፣ ዐማራው የአገሩ ባለቤትነትን ዳግም ማረጋገጥ፣ የዐማራውን ሁለንተናዊ ማንነት ማረጋገጥ፣ ለእነዚህ ሁሉ ዕውን መሆን በትግሬ-ወያኔና በኦነግ ትብብር የአገሪቱንና የሕዝቡ ገዥ ሕግ የሆነውን ሕገ-መንግሥትና ሥርዓቱን ከሥሩ ማፍለስና ዐማራ እንዴ ሌሎች ማኅበረሰቦች በእኩልነት የሚሳተፍበት ዴሞክራሲያዊ ሕገመንግሥትና ሥርዓት መዘርጋት ነው።

ለነዚህ ተግባሮች ዕውን መሆንም ዐኅኢአድ ከምሥረታው ጊዜ ጀምሮ የጥቃቱ ሰላባ የሆነውን የዐማራ ሕዝብ እየተፈጸመበት ስላለው የዘር ዕልቂት ከማሳወቅ ባሻገር፣ በነገዱ ዙሪያ ራሱን አደራጅቶ ኅልውናውና በማስጠበቅ፣ ለኢትዮጵያ አንድነት መጠበቅ የራሱን ነባር ታሪካዊ ሚናውን እንዲጫወት የበኩሉን ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል። በዚህም መሠረት በአገር ቤት የድርጅቱ አባላትና ደጋፊዎች ቁጥር በአጭር ጊዜ ውስጥ ከምንጠብቀው በላይ ዕድገት አሳይቷል። በውጭም የድርጅቱን ዓላማ ከማሰራጭት በተጓዳኝ የሰው ኃይል አቅሙን ለማጎልበት የሚችለውን እያደረገ ነው። በውጭ የተደራጁ የዐማራ ፖለቲካ ድርጅቶች፣ የሙያ ማኅበራት፣ የሲቪክ፣ የየአካባቢ ማኅበራትን የብዙኃን መገናኛ ዘዴዎች ባንድነት ሁለንተናዊ አቅማቸውን አቀናጅተው ለዐማራው የማይበገር ኃይል እንዲሆን ታሳቢ አድርጎ የተመሠረተው«የዐማራ ድርጅቶችና ማኅበረሰብ ስብስቦች» በአጽሕሮተቃል «ዐድማስ» በሚሰኘው ስብስብ ዐኅኢአድ የበኩሉን ሚና እየተጫወተ ይገኛል።

ዐኅኢአድ ለዐማራው ኅልውና መጠበቅ፣ ዐማራው ራሱን አደራጅቶ የማንነቱ ጠበቃና ጋሻ እንዲሆን አቅም እና ሁኔታዎች የፈቀዱትን እያደረገ መጓዝ፣ በማኅበረሰቡ ውስጥ ሁነኛ ቦታ እንዲይዝ በማድረጉ፣ የትግሬ-ወያኔው ጭንብል የሆነው ኢሕአዴግ የተሰኘው አገርና ሕዝብ አጥፊ ስብስብ እንደ ድሮው ሕዝቡን ለመግዛትና አስገድዶ የፍላጎቱ ተገዥ የማድረግ አቅሙን ጥያቄ ውስጥ ጥሎታል። ይህም በመሆኑ፣ ባለፉት ሦስትና ሁለት ዓመታት ለሁለት ጊዜ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ እንዲያውጅ ከማስገደዱም በላይ፣ የአመራር ለውጥ እንዲያደርግ እንደተገደደ አይተናል።

በኦሮሞ ብሔርተኞች ሁለንተናዊ ትብብር፣ ከሁሉም በላይ በኦሕዴድና በቄሮዎች መካከል የተካሄደው የተናበበ ፀረ-ወያኔ እንቅስቃሴ፣ የኦሕዴድ አመራር በኢሕአዴግ ውስጥ ላለፉት 27 ዓመታት በወያኔ የበላይነት ተይዞ የነበረውን የወሣኝነት ቦታ እንዲለቅ ተገደል። ይህም የኦሕዴዱ ዶ/ር ዐቢይ አሕመድ ወደ አገሪቱ ወሳኝ የፖለቲካ ማዕከል ቦታን እንዲጨብጡ አድርጓል። የዐቢይ የአገሪቱ ዕጣ ፈንታ ወሣኝ ወደ ሆነው የሥልጣን ማማ ላይ መውጣት የአገሪቱን የተወጣጠረ ፖለቲካና ወደ እርስ በርስ ፍጅት እያመራ ባለው የፖለቲካ አየር ውጥረት እንዲረግብ የማድረግ አዝማሚያ እንዲከተል እያደረገው እንደሆነ ይስተዋላል።

ዶ/ር ዐቢይ፣ የጠቅላይ ሚንስትርነቱን ኃላፊነት ሲረከቡ ያደረጉት ንግግር ከኢሕአዴግ የ27 ዓመታት ጉዞ የተለየ ኢትዮጵያዊነትን፣አንድነትን፣ ይቅርታን፣ መቻቻልን እና አብሮነት መነሻና መድረሻ ያደረገ ሀሳብ ማራመዳቸውን አስተውለናል። በማከታተልም በአምቦ፣ መቀሌ፣ ጎንደር፣ ባሕር-ዳር፣ ቤንሻጉል-ጉምዝ፣ ጋምቤላ ከሕዝብ ጋር ባደረጉት ንግግርና ከሕዝቡ ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች የሰጡት መልስ፣ ዐማራው ለገጠሙት ችግሮችና ላነሳቸው ጥያቄዎች ግልጽ መልሶች ካንደበታቸው ባይሰሙም፣ በጥቅሉ ያራመዷቸው ሀሳቦች በተለይም የክልል ተብዮዎችን ድንበሮች ጉዳይ የሚያጠና ኮሚሽን ይቋቋማል ያሉት የዐማራው ጥያቄ የሆኑትን ግዛቶች አብሮ የሚያይ ስለሚሆን፣ በዚህ ረገድ ጥያቄውን አጠናክሮ መቀጠል ከእኛ የሚጠበቅ ይሆናል።

በሌላ በኩል በፓርላማው ያቀረቡት ሀሳብና ከሁሉ በላይ የትግሬ-ወያኔ አባላት ከሆኑት የፓርላማ አባላት ለተጠየቁት ጥያቄ የሰጡት መልስ፣ በተለይም «አሸባሪ ማነው? የሚል ጥያቄ አንስተው አሸባሪዎች እኛ ነን፤ አሸባሪው መንግሥት ነው። ሕገመንግሥቱ የተያዘን ሰው ግረፍ፣ ደብድብ፣ አካል አጉድል የሚል የለም። በመላ አገሪቱ ከወረዳ እስከ ፌደራል ድረስ ፖሊስ ሲገርፍና ሲያሰቃይ የነበረው ሕገመንግሥታዊ አይደለም። ያን ያደረገ ፖሊስ አሸባሪ ነው። በተሐድሶ ስብሰባው ኢሕአዴግ ራሱን ፈትሾ ይቅርታ ጠቅቋል። ይቅርታ መጠየቁ ስሕተት መሥራቱን ማመኑ ነው። እኔም የጠቅላይ ሚኒስትርነቱን ኃላፊነት ሲሰጠኝ በፓርላማው ፊት ይቅርታ ጠይቄአለሁ። እስከሁን የተጓዝንበት ጉዞ ከችግር አላወጣንም። ሁሉም ነገር በዘር ሆኗል። ሌላው ቀርቶ የሃይማኖቱ ክፍፍል በዘር ነው። ከውስጥና ከውጭ ያለው ሲኖዶስ ከጀርባው ዘር አለ። በዚህ መንገድ ኢትዮጵያን ማዳን አይቻልም» በማለት የሰጡዋቸው መልሶች የትግሬ-ወያኔ ላለፉት 44 ዓመታት ገደማ የተጓዘበትን የጥፋት ጎዳና የኮነነና ኢትዮጵያዊነትን ማዕከል ያደረገ አዲስ ጎዳና መከተል እንዳለብን ያሳሰበ ነው። ይህም ዶ/ር ዐቢይ ከትግሬ-ወያኔና ተላላኪዎቹ ከሚያራምዱት ዓላማ ጋር ፍፁም ተቃራኒ በመሆኑ፣ የትግሬ-ወያኔ የቆመበትን መሠረት ከሥሩ ንዶበታል። ይህም ለትግሬ-ወያኔው ቡድን የእግር እሣት፣ የመሀል ሆድ ቁርጠት ሆኖበታል።

በሌላ በኩል አዋሳና ውልቂጤ ላይ ያደረጓቸው ንግግሮች ከሕዝብ ለቀረቡ ጥያቄዎች የሰጡዋቸው መልሶች፣ ወያኔንና ተላላኪዎቹን እጅግ ያስበረገገ ከመሆን አልፎ፣ በወላይታና በሲዳማ፣ በጉራጌና ቀቤና ነገዶች መካከል ችግር እንዲፈጠር ያደረጉ ቡድኖችና ግለሰቦች ያለምንም ቅድመ ሁኔታ በራሳቸዉ አነሳሽነት አሁን ከያዙት ሥልጣን እንዲለቁ መጠየቃቸዉና እነሁ አጥፊዎች ለፍትሕ ይቀርባሉ ሲሉ ያስደመጡት ቁርጠኛ ሀሳብ የትግሬ-ወያኔው ምሽግ በደቡብ ኢትዮጵያ ባሕር የገባ ጨው እንዳደረገው እየተስተዋለ ነው።

በጥቅሉ ዶ/ር ዐቢይ፣ ሥልጣን በጨበጡ ሁለት ወር ውስጥ እያከናወኑት ያሉት ሕዝብን የማረጋጋት፣ ውጥረትን የማላላት፣ ተስፋን የመፈጠቅ፣ አንድነትንና አብሮነትን የመስበክ፣ ኢትዮጵያዊነትን የማጉላት ተግባሮች ይበሉ! ይግፉ! የሚባልላቸው ሀሳቦች ናቸው። የዐማራ ኅልውና ለኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (ዐኅኢአድ) እንደ ተቃዋሚ ድርጅት፣ ሕዝቡና የተደራጁ የማኅበረሰቡ ክፍሎች በትግላቸው የራሳቸው ያደረጓቸውን ድሎች የትግሉ ውጤቶች እንደሆኑ በማመን፣ በነርሱ መሠረትነት ለቀሪዎቹ የሕዝብ ጥያቄዎች መመለስ ትግሉን አጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት ያምናል። ስለሆነም፣ ዐኅኢአድ አባላትና ደጋፊዎች፣ የዐማራው ጥያቄ ተመልሷል የምንለው፣ ዐማራውን አገር አልባ ያደረገው ሕገመንግሥት ተብየ ተሽሮ፣ በዜግነት ማንነት ላይ የተመሠረተ ሕገመንግሥት በሕዝቡ ቀጥተኛ ተሳትፎ ሲረቀቅና ሲጸድቅ፣ የትግሬ-ወያኔ የዘረጋው ከፋፋይና ዘረኛ ፖለቲካዊ ሥርዓት ሲሻርና ሕዝቡ የኔ በሚለው ፖለቲካዊ ሥርዓት ሲተካ፤ በዐማራው ላይ የዘር ዕልቂት የፈጸሙ ግለሰቦችና ቡድኖች ለፍትሕ ሲቀርቡ፣ የተፈናቀሉ ዐማሮችና ሌሎች ኢትዮጵያውያን አስፈላጊው ካሣ ተከፍሎአቸው ወደ ነበሩበት ቦታ

ሲመለሱ ነው። ለዚህ ዕውን መሆንም ሕዝብን ማዕከል ያደረገ፣ ሁሉንም በኢትዮጵያ ጉዳይ ያገባናል የሚሉ ከግለሰብ እስከ ማኅበረሰብ ያሉ የተደራጁ አካሎች ተሳታፊ የሚሆኑበት የሽግግር መንግሥት ሲመሠረትና፣ የሽግግር መንግሥቱ የሕዝቡ ፍላጎት መገለጫ የሆነ ፖለቲካዊ ሥርዓት ሲዘረጋና፣ የፖለቲካ ድርጅቶች በዕኩል ሜዳ እና ዳኝነት ተወዳድረው፣ በሕዝብ ድምፅ አሸናፊ የሆነው ፓርቲ ወይም ድርጅት ሥልጣኑን እንዲረከብ ሲደረግ ነው።

ከዚህ አንፃር ፣ የዐማራ ኅልውና ለኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት አባሎችና ደጋፊዎች፣ ዶ/ር ዐቢይ እያራመዷቸው ያሉ ቀና ሀሳቦችን በመደገፍ፣ ለተሟላ የዐማራ ሕዝብ ጥያቄዎች ሙሉ መልስ ለማስገኘትና ለኢትዮጵያዊነት ዳብሮ መቀጠል አስፈላጊ የሆኑ ሁኔታዎች በተከታታይ እንዲከወኑ ከላይ የተዘረዘሩትን የሕዝብ ጥያቄዎች አጠናክሮ መጠየቅ፣ ለእነዚህም ተግባራዊ መሆን የሚበጁ የትግል ስልቶችን፣ አማራጭ ሀሳቦችን በማቅረብ በአገዛዙ ላይ ተጽዕኖ ማሳደር ይጠበቅባቸዋል። ተቃዋሚ ወይም በዐቢይ አባባል ተፎካካሪ ድርጅቶች ዋና ተግባራቸው፣ በሥልጣን ላይ ያለው ድርጅት የሚሠራቸውን ተገቢና ትክክል ያልሆኑ ድርጊቶችን ሕዝቡ እንዲቃወማቸው ማመላከት፣ ለአገሪቱና ለሕዝቡ ይጠቅማል ያላቸውን አማራጭ ሀሳቦች ማቅረብና ሕዝቡ የእኔ እንዲላቸው ማድረግ ነው። በትግል የተገኙትን ድሎች የሕዝቡ እንደሆኑ በማስረገጥ፣ ቀሪዎቹ ጥያቄዎች እንዲመለሱ የተጠናከረ ግፊት ማድረግ ነው። ስለሆነም የዐማራ ኅልውና ለኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት አባሎችና ደጋፊዎች፣ ዶ/ር ዐቢይ እስካሁን ያደረጓቸውን መልካም ነገሮች በሕዝቡ ግፊት ዕውን የሆኑ፣ የሕዝቡ የትግል ፍሬዎች መሆናቸውን በመቀበል፣ ለቀሪዎቹ ጥያቄዎች መሟላት ሁለንተናዊ ብቃትን በማጎልበት በአመራሩ ላይ አዎንታዎ ተጽዕኖዎችን መፍጠር በይደር የሚያዝ ጉዳይ አይደለም። የዐማራው ጥያቄዎች የሚመለሱት በማንም ሳይሆን በራሱ የዐማራው ትግል ነው። ለዚህም አማራጭ ሀሳቦችንና የትግል ሥልቶችን በማፍለቅ፣ በአገዛዙ ላይ ወጥና ተካታታይ ተጽዕኖ ማሳደር ይገባል።

የዐማራ ኅልውና መጠበቅ፣ ለኢትዮጵያ አንድነት መጠበቅ ዋስትና ነው!

ዐማራው በልጆቹ ትግል ኅልውናውን ያስጠብቃል!